# ባለ አንቀልባው ትግል

ከአሊ ሁሴን

ሠኞ ተመስርቶ፣
ማክሰኞ መግለጫ፣
ሠው የለው በባዶ፣
ቢሮ መቀመጫ፣
ረቡዕ የጦር አዋጅ፣
ሐሙስ ፍልሚያ ጠሪ ፣
አርብ ገንዘብ አምጡ፣
ሠራዊቱ እሱ፣
እሱው የጦር መሪ ፣
ቅዳሜ ደግሶ፣ ጮማውን ገርዳፊ፣
ዕሁድ ፓልቶክ ገብቶ፣
ሀሰቱን ለፍላፊ፣
በአንድ ሳምንት አብጦ፣
እንደ ልደት ፊኛ፣
ከፊት ተደንቅሮ፣
ሠው የለም ያለእኛ፣
ባዩ እያስቸገረ፣
ትግሉ ተራዝሞ፣
ከትከት ብሎ ይስቃል፣
ጠላት ከፊት ቁሞ።

በዱር በገደሉ፣

ጠላትን ተጋፍጦ፣

አልገዛም ማለት፣

ጠመንጃ ጨብጦ፣

የፋሮች ሆነና፣

ፈንኖ መሸፈት፣

በአምስት መቶ ዶላር፣

ሸምቶ አርበኝነት ፣

ፒሳው ሜዳ ሆኖ፣

መለኪያ ጥይቱ፣

ባለ ሀምበርገር ቦንቡ፣

ተቀምጦ ከቤቱ ፣

ያለባሩድ ሽተታ፣

በሳይበር ቀረርቶ፣

አርባ ተፊ ምላስ፣

አዝማች አዘጋጅቶ፣

ተኳሹ በዛና፣

ገዳይ ከሩቅ መትቶ፣

ድል ሽቅቡን ያዘ፣

መጠጋቱን ትቶ፣

ምሁሩም ብር ነክሶት፣

እራሱ አባብጦ፣

ማየቱ ተስኖት፣

ሆዱ ተለጥጦ፣

ያልነበረው ነበርኩ፣

ያልዋሰው እየዋሰ፣

ባንዳ አክሊሉን ጭኖ፣

ሰው እያመገለ፣

ባንቀልባ እሹሩሩ፣

ትግላችን ሆነና፣

እጥፍ ድርብ ሆነ፣

ያለብን ፈተና።